በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ተገመ/ገ/29/16
Ref.No
ቀን 28/6/2016
Date

Geez Laws & Business

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የውጪ ምንዛሬ ፈቃድ ክልከላ በተደረገባቸው እቃዎችና ተሽከርካሪዎች ላይ ማስተካከያ ይመለከታል፤</u>

የውጭ ምንዛሬ ለመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች፣ ለመድሃኒትና ለህክምና መሳሪያዎች፣ ከውጭ ገብተው በአገር ውስጥ እሴት ተጨምሮባቸው ገቢ ምርቶችን ለመተካት የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ለሚውሉ ግብዓቶች፣ የካፒታል እቃዎችን፣ ወዘተ ለማስገባት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መንግስት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው ዝርዝር እቃዎችና ተሽከርካሪዎች ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሂ1/7/252 በቀን 04/02/2015 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለአፈጻጸም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ለጉምሩክ ኮሚሽን ተላልፎ በስራ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

ይህን ተከትሎ ጉምሩክ ኮሚሽን በቀን 17/04/2016 ዓ.ም በቁጥር 4/0429/16 በተጻፈ ደብዳቤ በጠየቀው እና መንግስት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት የውጭ ምንዛሬ ክልከላ ከተደረገባቸው እቃዎች ጋር ተያይዞ በአፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመዳሰስና በመለየት የሚከተለው ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

1. ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሂ1/7/252 በቀን 04/02/2015 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በሠንጠረዥ የተገለጹት የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው ዝርዝሮች በሕግ በተደነገገ ፍራንኮ ቫሉታ የሚገቡ እቃዎችን እና ተሽከርካሪዎችን የማይመለከት መሆኑን፤

2. ከመጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት የባንክ ፈቃድ የተሰጠባቸው እቃዎች እና ተሽከርካሪዎች በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል የሚቀርቡ ሠነዶች አስፈላጊው ማጣራት እየተደረገባቸው ለመጨረሻ ጊዜ በመሸጋገሪያ እንዲገቡ፤

3. ተሽከርካሪዎች ጎረቤት አገር ወደብ ወይም ጉምሩክ ጣቢያ በደረሱበት ጊዜ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር 1287/2015 አንቀጽ 2(24) ለአዲስ ተሽከርካሪ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟሉ ሆነው ነገር ግን ይህን ውሳኔ ሲጠብቁ የተሽከርካሪው እድሜ ያገለገለ ምድብ ውስጥ የገባባቸው ከሆነ በክልከላው ምክንያት በጎረቤት አገር ወደብ ወይም በጉምሩክ ጣቢያ

ስልክ 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.BOX 1905, 1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

https://t.me/GeezLaws



የቆዩበት ጊዜ ሳይታሰብ እድሜው ጎረቤት አገር ወደብ ወይም የጉምሩካ ጣቢያ እስከደረሰበት ያለውን ጊዜ ድረስ ብቻ በማስላት እንዲስተናገዱ፤

4. የቀረጥ ነፃ ሱቆች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች የውጭ ምንዛሪ ክልከላው እንዳይመለከታቸው፤
5. ከታች በሠንጠረዥ የተመለከቱ ዝርዝሮች አፈጻጸማቸው በእቃው ዓይነት መግለጫ መሰረት እንዲሆን፤
6. ተሽከርካሪን ሳይጨምር የውጭ ምንዛሬ ክልከላው የሚመለከተው እቃዎቹ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ዝግጅት ሳይደረግባቸው ወይም የምርት ሂደት ሳይከናወንባቸው ወደ አገር በገቡበት ሁኔታ በቀጥታ ጥቅም (አገልግሎት) ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁ ምርቶችን ብቻ ሲሆን፤ ማናቸውንም ለምርት ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ወይም ግብዓቶችን ክልከላው የማይመለከት መሆኑን፤
7. ተሽከርካሪን በሚመለከት ከተዘጋጀው በከፊል የተበተነ (SKD) ወይም ሙሉ በሙሉ የተበተነ (CKD) መስፈርት በታች የሆኑ (መስፈርቱን የማያሟሉ) ከሆነ የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው መሆኑን፤

እየገለጽን፤ ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሂ11/7/252 በቀን 04/02/2015 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ እና በተለያየ ጊዜ የተሰጡ ማብራሪያዎች ተሽረው በዚህ የተተኩ ሲሆን፤ በአፈጻጸም ወቅት ሲያጋጥሙ የነበሩ ችግሮች ከላይ በቀረበው ማብራሪያ እና አባሪ በተደረገው 03 ገጽ ማስተካከያ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

<u>ግልባጭ:-</u>

- ለትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
- ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

https://t.me/GeezLaws

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

| ተ.ቁ | የታሪፍ ምዕራፍ/አንቀፅ/ቁጥር | የዕቃ ዓይነት መግለጫ | Product Description |
|---|---|---|---|
| | | ውጤቶች፣ ኒኮቲን ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፤ ሌሎች ኒኮቲን ያላቸው ውጤቶች ሊኮቲን ወደ ሰው አካል ለማስረጽ ታስቦ የተዘጋጁ | combustion; other nicotine containing products intended for the intake of nicotine into the human body |
| 13 | 2501.0010 | የገበታ ጨው | Table salt |
| 14 | 33.03 | ሽቶዎችና ቶይሌት ዎተርስ | Perfumes and toilet waters |
| 15 | 3304.1000፣ 3304.2000፣ 3304.3000 | የከንፈር ቀለም፣ የዓይን መኳኳያ፣ የእጅ ወይም የእግር ማሳመሪያ | Lip make-up, Eye make-up, Manicure or Pedicure |
| 16 | 3401.1100፣ 3401.1900፣ 3401.2090 | ሣሙና | Soap |
| 17 | 36.04 | ርችቶች | Fireworks |
| 18 | 42.02 | ቦርሳ እና ዋሌት | Bag and Wallet |
| 19 | 49.09 | የታተሙ ሥዕላዊ መግለጫ ያላቸው ካርዶች | Postcards and Similar Cards |
| 20 | 49.10 | የቀን መቁጠሪያ ካሌንደሮች | Calendars |
| 21 | 4911.9190 | ስዕሎች የግድግዳ ስዕልን ጨምሮ | Pictures including wall pictures |
| 22 | ምዕራፍ 57 | ምንጣፎች | Carpets |
| 23 | 65.04 እና 65.05 | ክፍያዎችና ባርኔጣዎች | Hat and Headgear |
| 24 | 66.01 | ዣንጥላዎች | Umbrella |
| 25 | 67.02 | አርቴፊሻል አበባዎች | Artificial flowers |
| 26 | 67.03 እና 67.04 | የሰው ፀጉር፣ የእንስሳት ፀጉር እና አርቴፊሻል ፀጉር | Human Hair, Animal Hair and Artificial Hair |
| 27 | ከ69.11 እስከ 69.14 | ከፖርሲሊን እና ከሴራሚክ የተሠሩ የወጥ ቤት እቃዎች | Porcelain and Ceramic kitchenware |
| 28 | 70.13 | ከብርጭቆ የተዘጋጁ የመጠጥ መጠጫ እቃዎች፣ የሲጋራ መተርኮሻዎች፣ የአበባ | Drinking glasses, Ash tray, Vase |

Ministry of Finance ARCHIVES

ስልክ
251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.BOX 1905, 1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

Geez Laws & Business

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ቁጥር ___________
Ref.No
ቀን ___________
Date

| ተ.ቁ | የታሪፍ ምዕራፍ/አንቀፅ/ቁጥር | የዕቃ ዓይነት መግለጫ | Product Description |
|---|---|---|---|
| | | መያዣ | |
| 29 | 71.17 | አርቲፊሻል ጌጣጌጦች | Artificial jewelry |
| 30 | 87.03 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞው የቀረቡ የቤት አውቶሞቢል እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች (በኤሌክትሪክ ሞተር የሚሰሩ፣ ሀይብሪድ ተሽከርካሪዎችን እና አምቡላንሶችን ሳይጨምር/ | Completely Built Up (CBU) Automobiles and three wheelers (except electric motor, hybrid vehicles and Ambulance) |
| 31 | 87.11 | ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞው የቀረቡ ሞተር ሳይክሎች (በኤሌክትሪክ ሞተር የሚሰሩትን ሞተር ሳይክሎች ሳይጨምር) | Completely Built Up (CBU) Motorcycles (except electric motor Motorcycles) |
| 32 | 87.12 | ሳይክሎች | Bicycles |
| 33 | ምዕራፍ 91 | የእጅ፣ የጠረጴዛ እና የግድግዳ ሰዓቶች | Hand watches, Table and Wall clocks |
| 34 | 94.01 እና 94.03 | የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች (ክፍሎች በስተቀር) | Household and Office furniture (Except parts) |
| 35 | 95.04 እና 95.05 | የተለያዩ መጫወቻ ዕቃዎች፤ የበዓል፣ የካርኒቫል፣ የመዝናኛ፣ የአስማት እና መቀለጃ እቃዎች | Different games; Articles for Festive, Carnival, Entertainment, Conjuring, Novelty jokes |
| 36 | 96.13 | ጋዝ ላይተር | Gas Lighters |
| 37 | 96.15 | የፀጉር ማያያዣ መርፌዎች፣ የፀጉር ማስያዣ፣ የፀጉር መጠቅለያ፣ የፀጉር ጌጣጌጥ፣ | Hair pin, Clip, Grips, Roller, Bow, Band, Pony tail, Tiara |
| 38 | 9618.0000 | የልብስ ማሣያ አሻንጉሊቶች | Mannequin |

Ministry of Finance ARCHIVES 6

ስልክ
251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.BOX 1905, 1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et